# በአማራ ክልል በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ 99 ሰዎች ተገድለዋል

By wazemaradio

NOV 29, 2016

ዋዜማ ራዲዮ- በአማራ ክልል በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ ቢያንስ 99 ሰዎች በመንግስት ሃይሎች መገደላቸውን አረጋግጫለሁ ሲል የኢትዮጵይ ሰብዓዊ መብቶች ፕሮጀክት ሰኞ ህዳር 19 ቀን 2009 ገለፀ፡፡ የሟቾች ቁጥር ከዚህ ሊጨምር እንደሚችል የገለፀው የፕሮጀክቱ ሪፖርት የሟቾችን ስም ዝርዝር በመግለጫው አካቷል፡፡

ሐምሌ 29 ቀን 2008 ዓ.ም ከተከናወነው የባህርዳር ከተማ የተቃውሞ ሰልፍ ጀምሮ የመንግስት ታጣቂ ሃይሎች በወሰዱት  እርምጃ ከ 50 በላይ የሚገመቱ ንፁሃን ዜጎች እንደተገደሉ የገለፅው የኢትዮጵይ ሰብዓዊ መብቶች ፕሮጀክት በክልሉ ከሚገኙ አስራ አንድ ዞኖች ስድስቱ ዞኖች የጎላ ተቃውሞ በመንግስት ላይ አድርገዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ፕሮጀክት በመንግስት ታጣቂዎች የተከናወነው ግድያ ጎንደር፣ባህርዳር፣ደብረታቦር፣ፍኖተሠላም፣ ፣ ደብረ ማርቆስ፣ወረታ፣ አዴት፣ ድብረወርቅ፣ ቻግኒ፣ቡሬ፣ ዳንግላ፣አይባ፣ አርማጭሆ፣ ዳንሸ፣ በአከር፣ ሻውራ እና ምስራቅ ጎጃምን አካቷል ብሏል፡፡

ማረጋገጥ እና መሰብሰብ ከተቻለው የሟቾች ቁጥር መካከል አብዛኛው ሟቾች የባህርዳር ከተማ ወጣቶች ሲሆኑ ጎንደር እና አርማጭህም እንደዚሁ የግድያው ሰለባው የከፍባቸው ከተሞች ናቸው፡፡

በክልሉ የተቃውሞ ተሳታፊዎች ላይ እርምጃ የወሰዱ የመንግስት ሃይሎች ተጠያቂ እንዲሆኑ ፣ ሰለደረሰውም የሰው ህይወት እልቂት በገለልተኛ ወገን ምርመራ እንዲደረግ እንዲሁም የኢትዮጵያ መንግስት የመብት ጥያቄ ያነሱ ዜጎችን ከማፈን እና ከግድያ በመቆጠብ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ፕሮጀክት ጠይቋል፡፡

« በአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ምክንያት የሕትመት ዘርፉ ተሽመድምዷል- ሳንሱር ተመልሷል

ዘንድሮ የሚጀመር የጋራ መኖርያ ቤት አደኖርም-የቤቶች ልማት ከፍተኛ የገንዘብ ቀውስ ገጥሞታል »

By wazemaradio

## RELATED POST

CURRENT AFFAIRS HOME

CURRENT AFFAIRS HOME

CURRENT AFFAIRS HOME

## CATEGORIES

About Wazema

Art and Culture

Benegerachin Lay-Discussion

Book Review

Current Affairs

Fake News alert

Home

Letter From Addis

News

PODCASTS

Talking points

Uncategorized

Video

Wazema Dossier

Wazema Forum

## WAZEMA MEDIA

Wazema Media is legally registered organization founded in 2014 by Ethiopian exiled journalists, currently based in Addis Ababa, Ethiopia.